# የአነጋውያኑ የምርጫ ቦርድ ወያኔያዊ ሸፍጥ!

የምርጫ ቦርድ ተብየው አዲሶቹ የወያኔ/አነግ ቅጥረኞች ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተብየው የምርጫ ሕግ ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅን ለማጸደቅ ባቀረበው መተዳደሪያ ደንብ ተፎካካሪ ፓርቲ እንዳይኖር ለማድረግ ወይም በእጅጉ ለማዳከም በማሰብ ሁለት ትላልቅ መሰናክሎችን አስቀምጧል፡፡

አንደኛው "የመንግሥት ሠራተኛ በተመራጭነት በሚሳተፍበት ወቅት ምርጫው እስኪጠናቀቅ ጊዜ ድረስ ከሥራ ከደሞዝና ከጥቅማጥቅሞች ውጭ እንዲሆን ይደረጋል!" የሚለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አንድ ፓርቲ በፓርቲነት ለመመዝገብ ማቅረብ የሚኖርበትን የሕዝብ ፊርማ ለብሔራዊ (ለሀገር አቀፍ) ፓርቲዎች ከ1,500 ወደ 10,000 ያሳደገው ሲሆን ክልል ለሚሉት ደግሞ ከ750 ወደ 4,000 ማሳደጉ ነው፡፡

## ለተቃዋሚዎች እንቅፋትነቱ ምንድን ነው??? ከተባለ፦

አዲሷ ቅጥረኛ የምርጫ ቦርድ ሊቀመንበር ወ/ሮ (አለማግባቷን አውቃለሁ ነገር ግን ልጅ ስላላት የገለሞተች ሴት ወ/ት ስለማይባል ነው) ብርቱካን ሚዴቅሳ በመንግሥት ሠራተኞች ላይ ስለተጣለው ገደብ (የሙብት ገፈፋ) ፓርላማው ላይ ተጠይቃ ስትመልስ "የመንግሥት ሥራ እንዳይበደል ለማድረግ፣ የመንግሥት ሀብት መባከን ስለሌለበት!" የሚል ጨርሶ የማያሳምን መልስ ሰጥታለች፡፡ ይሄ መልስ የማያሳምን መሆኑ ያሳሰበው አገዛዙ ግን እነ ወ/ሮ ብርቱካን ሚዴቅሳ ከፓርላማ ከወጡ በኋላ ሌላ "የመንግሥት ተቋማት ከፓርቲ ወገንተኝነት ነጻ መሆን ስላለባቸው ተቋማቱን ከፓርቲ ወገንተኝነት ነጻ ለማድረግ፣ የመንግሥትንና የፓርቲን መቀላቀል ለማስቀረት፣ ኢፍትሐዊ ፉክክርን ለመከላከል ነው የመንግሥት ሠራተኛ በተመራጭነት በሚቀርብበት ጊዜ ከሚሠራው የመንግሥት ሥራና ከደሞዙ እንዲገለል የደነገግነው!" የሚል መልስ አዘጋጅቶ በመስጠት ፓርላማ ውስጥ ከሰጠችው መልስ ውጭ ማምሻውን በብዙኃን መገናኛዎቹ እንድትናገረው አድርጓል፡፡

ይሄም ምላሽ "የአሁኑ ይባስ!" የሚያሰኝ ነው፡፡ ምክንያቱም የመንግሥት ተቋማትን ከፓርቲ ወገንተኝነት ነጻ ማድረግ የሚቻለው ሥርዓት አበጅቶ ደንብ ቀርጾ ወይም ሕግ ደንግጎ በማገድና ሕጉንም ተፈጻሚ በማድረግ እንጅ ፈጽሞ "እመረጣለሁ!" ያለን ሰው ለአጭር ጊዜ ከሥራና ከደሞዝ በማግለል ወይም በማገድ አይደለምና ነው፡፡

እንደምታውቁት በወያኔ/ኢሕአዴግ ዘመን የመንግሥት ሥራዎች በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ በኢሕአዴግ አባላት የተያዘ ሆኖ ኖሯል፡፡ እንዲያውም ሰው ካልጠፋ በስተቀር የኢሕአዴግ አባል ያልሆነ ሰው የመንግሥት ሥራን ማግኘት አይችልም፡፡ ኢሕአዴግ አባላቱ ያልሆኑ በመንግሥት ሥራ እንዳይቀጠሩ ከማድረግም አልፎ ተቋማቱን መገልገያው አድርጎ ነው የቆየው አሁንም ድረስ፡፡ በዚህም ምክንያት አብዛኛው የመንግሥት ሠራተኛ የኢሕአዴግ አባል ነው፡፡

ያለው እውነታ ይሄ በሆነበት ሁኔታ ማለትም የመንግሥት ተቋማት ከሞላ ጎደል በኢሕአዴግ አባላት የተሞሉ በሆኑበት ሁኔታ "የመንግሥት ተቋማት ከፓርቲ ወገንተኝነት ነጻ መሆን ስላለባቸው ተቋማቱን ከፓርቲ ወገንተኝነት ነጻ እንዲሆኑ ለማስቻል ነው የመንግሥት ሠራተኛ በተመራጭነት በሚቀርብበት ጊዜ ከሚሠራው የመንግሥት ሥራና ከደሞዙ እንዲገለል የደነገግነው!" የሚለው መልስ ሲበዛ ምጸትና ሕዝብን መናቅ ነው፡፡

የምርጫ ቦርድ ሥልጣኑን፣ ኃላፊነቱንና ግዴታውን ለመወጣት በማሰብ የመንግሥት ተቋማትን ከፓርቲ ወገንተኝነት ነጻ የማድረግና ተቋማቱን የፓርቲ መገልገያና ጥቅም ማስከበሪያ ከመሆን ነጻ ለማድረግ ካሰበ ከምንም ነገር አስቀድሞ ማድረግ የሚጠበቅበት ዐቢይ ጉዳይ ሊደረግ ከታሰበው ምርጫ በፊት ፈጥኖ መውሰድ ያለበት እርምጃ የመንግሥት ተቋማትን የፓርቲ ወገንተኛ ማድረግ፣ የፓርቲ መገልገያና ጥቅም ማስከበሪያ ማድረግ ፈጽሞ የተከለከለና ወንጀል መሆኑን በግልጽና በደማቁ የሚገልጽ ሕግ መደንገግና ወያኔ/ኢሕአዴግ የመንግሥት ተቋማትን በአባላቱ እንዲያዝና እነኝህን የመንግሥት ተቋማትንም ከፓርቲው መገልገያና ከፓርቲው ጥቅም ማስከበሪያ መሣሪያነት ነጻ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ሕገወጥ ድርጊቱን ማስቆም ይጠበቅበታል፡፡

እስከአሁን ባለው ጊዜ በፖለቲካ ፓርቲዎች "የመንግሥት ተቋማት ከፓርቲ ወገንተኝነት ነጻ መሆን አለባቸው፣ የመንግሥት ተቋማትን የፓርቲ መገልገያና የፓርቲ ጥቅም ማስከበሪያ ማድረግ ሕገወጥና ኢፍትሐዊ አሠራር ነው!" እየተባለ የሚነገረው በምዕራቡ ዓለም ካለው ልምድ በመነሣት ወይም በመውሰድ ነው እንጅ ይሄንን የሚከለክል በግልጽና በደማቁ ተብራርቶ የተደነገገ ሕግ በሀገሪቱ የለም፡፡ ሕግ በሌለበትና ተፈጻሚ ባልተደረገበት ሁኔታ ይሄንን ሕገወጥ ተግባር መከላከልም ሆነ ማስቆም አይቻልም፡፡

ያለው ሐቅ ይሄ በሆነበትና ወያኔ/ኢሕአዴግ ሕገወጥ ተግባሩን፣ ኢፍትሐዊ አሠራሩን እንዲያቆም፣ የመንግሥት ተቋማቱም ነጻ እንዲሆኑ ባልተደረገበት ሁኔታ "የመንግሥት ተቋማት ከፓርቲ ወገንተኝነት ነጻ መሆን ስላለባቸው ተቋማቱን ከፓርቲ ወገንተኝነት ነጻ እንዲሆኑ ለማስቻል ነው የመንግሥት ሠራተኛ በተመራጭነት በሚቀርብበት ጊዜ ምርጫው እስኪጠናቀቅ ጊዜ ድረስ ለጊዜው ከሚሠራው የመንግሥት ሥራና ከደሞዙ እንዲገለል የደነገግነው!" ብሎ ማለት ግልጽ ምንደኝነት (double standard) ነው፡፡

ሲጀመር አንድ የመንግሥት ሠራተኛ የፈለገውን የፖለቲካ አቋም መያዝና ማራመድ መብቱ ነው፡፡ መብቱ ያልሆነውና የማይችለው ነገር ይሄንን ፖለቲካዊ አቋም በመንግሥት ሥራው ላይ ማንጸባረቅና ሥራውን ለፖለቲካዊ አቋሙ መጠቀሚያ መገልገያ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ፖለቲካዊ አቋም የመያዝ መብቱ ሕገመንግሥታዊ መብቱ ከሆነና በመንግሥት ሥራ ላይ መሆኑ የፈለገውን ፖለቲካዊ አቋም ከመያዝና ከማራመድ እንዲከለከል ካላደረገው ለተመራጭነት በሚቀርብበት ጊዜ ገደብ ለመጣል መሞከር ኢፍትሐዊ፣ ኢአመክንዮአዊ አሠራርና ግልጽ የመብት ገፈፋ ነው፡፡

ወይ ደግሞ መሆን ያለበት ባጠቃላይ የመንግሥት ሠራተኛ የተባለ ሁሉ በመንግሥት ሥራ ባለበት የሕይወት ዘመኑ ፖለቲካዊ አቋም መያዝና ማራመድ የማይችልና የተከለከለ ማድረግ ነው፡፡ ይሄንን ማድረግ ደግሞ ሰብአዊና የዜግነት መብት የሆነውን መብት መገፈፍ ሊሆን ነው፡፡ ስለሆነም የመንግሥት ተቋማትን ከፖለቲካ ወገንተኝነትና የፓርቲ መገልገያ የጥቅሙም ማስከበሪያ ከመሆን መከላከል የሚቻለው ለፓርቲዎችም ሆነ ለግለሰቦች በመንግሥት ሥራ ቦታ የፖለቲካ አቋምን ማራመድ፣ ማንጸባረቅና የመንግሥት ሥራውን ለፖለቲካዊ አቋሙ መገልገያ መጠቀሚያ እንዳያደርግ በሕግ በመከላከል እንጅ በተመራጭነት በሚቀርብበት የምርጫ ወቅት ለአጭር ጊዜ ከሥራና ከደሞዝ ውጭ እንዲሆን በማድረግ አይደለም፡፡

ስለዚህም በግልጽ መረዳት እንደሚቻለው ይሄንን ገደብ ማስቀመጥ የተፈለገበት ምክንያት የተቃዋሚዎችን አቅም ለማዳከምና ከምርጫ ውጭ ለማድረግ በማሰብ ነው ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ሌሎች ሕጎች በወያኔ/ኢሕአዴግ ተመራጮች ላይ ተፈጻሚ እንዳልሆኑ ሁሉ ይሄም ሕግ በወያኔ/ኢሕአዴግ ተመራጮች ላይም ተፈጻሚ አይሆንምና ነው፡፡ ይሆናል ቢባልም እንኳ ደሞዙ በኢሕአዴግ እንዲሸፈን ያደርጋሉ፡፡ ሌሎቹ ፓርቲዎች ግን ይሄንን የማድረግ አቅም ስለሌላቸው ማንም ሰው ደሞዙንና ሥራውን አጥቶ ተመራጭ ሊሆንላቸው የሚችል የመንግሥት ሠራተኛ ሊያገኙ አይችሉም ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ይሄ አንቀጽ ኢፍትሐዊ ፉክክርን በማስፈን ወያኔ/ኢሕአዴግን ተጠቃሚ የሚያደርግ እንጅ ወ/ሮ ብርቱካን እንዳለችው ፍትሐዊ ፉክክርን የሚያሰፍን አይደለም፡፡

ወደ ሁለተኛው ነጥብ ሳልፍ እንደምታውቁት ባለው አፋኝና ፈላጭ ቆራጭ አንባገነን አገዛዝ ምክንያት ብሔራዊ (ሀገር አቀፍ) ፓርቲዎች ሲቋቋሙ ማቅረብ የሚጠበቅባቸውን ከሦስትና ከዚያ በላይ የተለያዩ ክልሎች ነዋሪ የሆኑ የ1500 ሰው ፊርማ ለማሰባሰብ ሕዝቡ ለተቃዋሚዎች መፈረም እጅግ ስለሚፈራ ይሄንን ያህል ሰው ፊርማ ማሰባሰብ ምን ያህል አስቸጋሪና የማይቻል ሆኖ እንደቆየ የሚታወቅ ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ ፓርቲዎች ከ1500 ሰው ፊርማው አብዛኛውን በአካል የሌለ ሰው ስምና ፊርማ እየሞሉ ቁጥሩን ሞልተው ሲያስገቡ እንደቆዩ የአደባባይ ምሥጢር ነው፡፡ ሕዝቡ ያለ ፍርሐት መብቱን መጠቀም የሚችልበት ምኅዳር ቢኖር ኖሮ 1500 ሰው አይደለም በመቶዎችና በሚሊዮኖች የሚቆጠር ሰው ቢያስፈልግ እንኳ የሚቸግር ባልነበረ፡፡

ቅጥረኛው የምርጫ ቦርድ አሁን ደግሞ ጭራሽ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ!" እንዲሉ ጭራሽ ፊርማውን ዐሥር ሽህ በማድረግ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የምርጫ ቦርድ ዕውቅናን ለማግኘት ማቅረብ ያለባቸውን የሕዝብ ፊርማ ፈጽሞ የማይቻል አድርጎታል፡፡ ሕዝቡ ለተቃዋሚዎች ሲፈርም በወያኔ ጥቃት ስለሚደርስበት በፍርሐት ምክንያት ሽህ አምስት መቶ ሰው ለማግኘት ፈጽሞ የማይቻል ሆኖ በቆየበት ሁኔታ ጭራሽ ዐሥር ሽህ ያውም ሙሉ የመኖሪያ አድራሻ ከነ ቤት ቁጥር ድርስ ተሞልቶ እንዲቀርብ መደንገግ ማንን ለመገፍተርና ማንን ተጠቃሚ ለማድረግ ታስቦ ቁጥሩ በጣም ከፍ እንዲል እንደተደረገ ግልጽ ነው፡፡ በዚህ በአዲሱ የምርጫ ቦርድ የፓርቲ ማስመዝገቢያ ሕግ ወይም ደንብ መሠረት አሁን ካሉት ፓርቲዎች ከወያኔ በስተቀር አንዳቸውም እንኳ አሟልተው ማቅረብ እንደማይችሉ እርግጠኛ ነኝ ብል ያጋነንኩ አይመስለኝም፡፡ እናም የእነ ወ/ሮ ብርቱካን ሸፍጥና ጉድ እዚህ ደረጃ ደርሷል ገናም አፋቹህን እስክትይዙ ድረስ ይቀጥላል፡፡

እነኝሁ አዲሶቹ የምርጫ ቦርድ አባላት የተባሉት "በሕዝብ ጥቆማ ተመረጡ!" ተብለው ከመሾማቸው በፊት ፓርቲዎች የምርጫ ማስፈጸሚያ የመግባቢያ ቃልኪዳን ሰነድ እንዲፈርሙ በተደረገበት ጊዜ ከወ/ሮ ብርቱካን ሚዴቅሳ ጋር ሆነው ሰነዱን ከማዘጋጀት ጀምረው ሥነሥርዓቱን እስከ ማስፈጸም ድረስ በወያኔ/ኢሕአዴግ ተመድበው ሲያገለግሉ የነበሩ እንደሆኑ ተቃዋሚዎች እያወቁ ከወራት በኋላ ወያኔ/ኢሕአዴግ እነኝሁን ቅጥረኞቹን "ቀጥተኛ በሆነ ግልጽ የሕዝብ ጥቆማ ተመረጡ!" ብሎ አምጥቶ የቦርድ አባላት ብሎ ሲሾማቸው ተቃዋሚዎቹ ያለ አንዳች ተቃውሞ ሞቅ ባለ ድጋፍ "እሽ መልካም!" ብለው ሲቀበሉ ነው አስቀድሞ ከነበሩ ማረጋገጫዎች በተጨማሪ ተቃዋሚ የሚባል አለመኖሩንና በሙሉ

የዘገምተኞች ጥርቅም መሆናቸውን ያረጋገጥኩት፡፡ እንኳንና ወሳኝ የሆነውን የመንግሥት ተቋማት የወያኔ/ኢሕአዴግ መገልገያና መጠቀሚያ እንዳይሆኑ የሚከለክል ሕግ እንዲወጣና ተፈጻሚ እንዲሆን ሊያደርጉና አስበው ሊሠሩ ይቅርና፡፡ አያሳዝንም ግን???

አምሳሉ  ገብረኪዳን